# ወልቂጤ ዩንቨርስቲ

## ማህበራዊ ሳይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

"ስንብት" ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት አንፃር

በ

ሂወት አበራ

ወልቂጤ ዩንቨርስቲ

ሰኔ 13/ 2014 ዓ.ም

# <<ስንብት>> ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት አንፃር

በ

ሂወት አበራ

የጥናቱ አማካሪ

መምህር ሄለን ገብረ ስላሴ

ለመጀመሪያ  ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ዩንቨርስቲ

ሰኔ 13/ 2014 ዓ.ም

## የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆነን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪዉ ስም ..................................................................................

ፊርማ________________________________

ይህ በተማሪ ሂወት አበራ "ስንብት"ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት አንፃር የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን የዩንቨርስቲዉ ጥራት ደረጃ የሟላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆነን ማረጋገጫ ነዉ።

ፈታኝ አንድ ------------------------------------------------------ ፊርማ

ፈታኝ ሁለት------------------------------------------------------ፊርማ

ቀን -------------------------------------------------

# ማዉጫ

ምስጋና ....... i
መታሰቢያነቱ ....... ii
አጠቃሎ ....... iii
ምዕራፍ አንድ ....... 1
1. መግቢያ ....... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....... 2
1.2 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ....... 2
1.3 የጥናቱ አላማ ....... 2
1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ ....... 2
1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ ....... 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 2
1.5 የጥናቱ ወሰን ....... 3
1.6 የጥናቱ ዘዴ ....... 3
1.7 የጥናቱ አወቃቀር ....... 3
1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ....... 3
ምዕራፍ ሁለት ....... 4
2. የንድፍ ሃሳብ ቅኝት ....... 4
2.1 ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት ....... 4
2.2 የፊልም ምንነት ....... 5
2.2.1 የፊልም ትወና አመጣጥ ....... 5
2 .3 የትወና ምንነት ....... 6
2.4 የተዋናይ ምንነት ....... 7
2.5 የፊልም ትወና ....... 7
2.5.1 ተመስጦ ....... 8
2.5.2 ዉስጣዊ ፍቺ ....... 8
2 .5 3 ስሜት ....... 8
2.5.4 ማስተዋል ....... 9
2.5.5 ድምጽ አወጣጥ ....... 9
ምዕራፍ ሶስት ....... 10
3. ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት ....... 10
3.1 የስንብት ፊልም ጭምቅ ታሪክ ....... 10
3.1.1 የስንብት ፊልም ተዋንያን ....... 11

3.2 የፊልም ትወና ........ 11
3.2.1 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ተመስጦ አንፃር ........ 11
3.2.2 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ዉስጣዊ ፍቺ አንፃር ........ 13
3.2.3 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ስሜት አንፃር ........ 14
3.2.4 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ማስተዋል አንፃር ........ 18
3.2.5 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ድምፅ አወጣጥ አንፃር ........ 19
ምዕራፍ አራት ........ 21
4. የማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች ........ 21
4.1 ማጠቃለያ ........ 21
4.2 የመፍትሔ ሀሳብ ........ 22
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ........ 23
ዋቢ መጽሐፍት ........ 24

# ምስጋና

አስጀምሮ ላስፈፀመኝ የድንግል ማርያም ልጅ ለሆነዉ ለመድሐኒያለም፣አምላክን ለወለደች ለድንግል ማርያም እና እናቴ ቅድስት አርሴማ እናተን ተስፋ አድርጌ አላፈርኩም እና ክብር ምስጋና ለናንተ ይሁን። አያየዋ አሁን ላለሁበት ህይወት መሰረት የሆንሽኝ አንቺ ነሽእና ምን  ባደርግልሽ ነዉ  ነብስሽን ደስ ማሰኛት?አመሰግናለሁ እናቴ ፈጣሪ ነብስሽን በአፀደ ገነት ያኑርልኝ እናቴ።አራታቹ የእናቴ ልጆች ብርቄ፣በእምነት፣ብቸኛዉ ወንድሜ ቴዲየ እና ቤዛየ ምበረታዉ  በናንተ ነዉ።ፈጣሪ እናንተን የመሰለ እህትቾ፣ ወንድም ስለሰጠኝ ይበልጥ አመሰገንኩት።ዕድሜና ጤና ይስጣቹህ ተስፋዎቼ።እንደእህት ሁና ደከመኝ፣ሰለቸኝ ሳትል ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ እዚህ እንዲደርስ ለረዳችኝ ለመምህርቴ ሄለን ገብረስላሴ ምስጋናየ ከልብ ነው መምህሬ።የግቢ ህይወትን አብራኝ ለተጋፈጠችዉ እና ይህን ጥናት በምሰራበት ጊዜ ጎኔ ሁና ላገዘችኝ ላበረታታችኝ አይዞሽ ባይ ጓደኛየ ስንታየሁ ፀጋዬ አመሰግንሻለሁ።ፈጣሪ ያሰብሽን በሙሉ ያሳካልሽ። እንዲሁም ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ  በምሰራበት ጊዜ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ፁሁፉን በ ኮምፒዉተር ላገዘችኝ ለ ራሄን ፈቀደ ክብር ምስጋና ላንቺ ይሁን ።

# መታሰቢያነቱ

ከሰዉ በታች ሁና አሳድጋ ፣ አስተምራ ያንዳችን ደስታ ሳታይ አርብ 28 /11/2010 ዓ.ም ድንገት በሞት ለተለየች ለእናቴ አዛኑ ጌጡ ( አያየ) ይሁንልኝ ።አያየዋ ህልምሽን አሳካዋለሁ።ነብስሽን በአፀደ ገነት ያኑርልኝ እናቴ...።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ የስንብትን ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት አንፃር በሚል የቀረበ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት አንፃር የተለያዩ መስፈርቶች አሉት።ከነእርሱም መካከል ተመስጦ፣ዉስጣዊ ፍች፣ ስሜት ፣ማስተዋል፣ድምፅ አወጣጥ ናቸዉ ።አጥኝዋ ከነዚህ ባህርያቶች ስንብትን ፊልም ተንትናለች ።የጥናቱ አላማ ስንብትን ፊልምን በትወናዉ ላይ የተስተዋሉ ደካማ እና ጠንካራ ጎን መዳሰስ ነዉ። አላማዉ ለማሳካትም የተጠቀመችዉ የጥናት አይነት ገላጭ የምርምር አይነት ሲሆን ስንብትን ፊልም ደጋግማ በማየት፣ከጥናቱ ጋር የማዛመዱ መፅሀፍት እና ጥናታዊ ፁሁፎችን በመዳሰስ፣ከድህረ ገፅ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በማሰባሰብ ስንብትን ፊልም ከከተመስጦ፣ውስጣዊ ፍቺ፣ስሜት፣ማስተዋል እና ከድምፅ አወጣጥ ትወና አንፃር ምን እንደሚመስል ተንትናለች። ስለሆነም ስንብት ፊልም የፊልም ትወና ባህርያቶችን የገመገመበት ነዉ ።

## ምዕራፍ አንድ

### 1. መግቢያ

ኪነ-ጥበብ የሰው ልጆች ማንነት ፣ማህበራዊ ሁኔታ ፣ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ፣ ባህል ፣ወግ ፣ልምድ ፣እምነት እንዲሁም የሰው ልጆች በሂወት ዘመኑ በሚያደርጋቸው የእለተእለት ገጠመኞች ውጣ ውረዶች..... ወዘተ በማዋህድ በፊልም ፣በቲያትር ፣በልቦለድ አማካኝነት ለተደራሲያን ባማረእና ታማኝነት ባለው መልኩየሚቀርብ ጥበብ ነው ፡፡ ኪነ - ጥበብ በውስጡ በርካታ ዘርፎች አካቶ የያዘ ሲሆን ከእነሱም መካከልም አንዱ ፊልም ነው ፡፡

ፊልም አንድን ታሪክ ተንቀሳቃሽ ምስልን በመጠቀም ሀሳብን ምናስተላልፍበት ታሪክን የምንነግርበት መንገድ ሲሆን ፊልም በአይን የሚታይ በጆሮ የሚደመጥ የጥበብ ዘርፍ ነዉ ። ፊልም በውስጡ በርካታ አለባዊያን አካቶ የያዘ ሲሆን ከእነሱ መካከል አንዱ ትወና ነዉ።

ትወና በድርጊት፣በድምፅ ፣ በእንቅስቃሴ የሚተወን ሙያ ሲሆን ስሜት ፣ድምፅ፣እንቅስቃሴ ተጨምሮበት ሊተላለፍ የተፈለገውን ስሜት ወይም መልዕክት በተገቢው መልኩ ለተመልካች ማሳየት ነዉ ፡፡ እንዲሁም የተሰጠን ታሪክ ህይወት ሰጥቶ ፣ ድርጊት ፣ እንቅስቃሴ ድምፅ በመጠቀም በተዋናይ አማካኝነት የሚሰራ የጥበብ ዘርፍ ሲሆን የትወና የጀርባ አጥንት የሆነዉ ተዋናይ ነዉ።

ተዋናይ በአንድ ድርሰት ውስጥ ያሉ ገፀ- ባህሪ ወክሎ የሚጫወት ወይም የሚተወን የትወና ባለሙያ ሰዉ ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚያጠናው ከፊልም ዝግጅት አለባውያን አንዱ የሆነው ትወና ላይ ነዉ፡፡ በሀገራችን ኢትዮጲያ በርካታ ፊልሞቸ ተሰርቷል ፡፡አሁንም እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ፊልሞች መካከል አንዱ «ስንብት» ነው፡፡

ስንብት ፊልም በአንተነህ ሃይሌ ደራሲነት እና አዘጋጅነት በዳኒ ቦይ ፊልም ፕሮዳክሽን በ2013 ዓ.ም በላባ ኢንተርቴመንት ለተመልካች የቀረበ የሀገራችን ፊልም ሲሆን ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ« ስንብት » ፊልም ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር በተገቢው ሁኔታ መጠቀሙን በመገምገም ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አጥኝዋ ‹ ስንብት › የተሰኘው ፊልም ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር ለመስራት ያነሳሳት ምክንያት ስንብት ፊልም ላይ ያሉ ተዋናዬቹ ገፀ_ባህሪዉን ተላብሰዉ በሚገባ ተዉነዉታል ወይ? የሚለዉን ሂሳዊ ትንተና መስጠት እና ስንብትን ፊልም ከተመሰጦ ፤ ከውስጣዊ ፍቺ፣ ከስሜት፣ ከማስተዋል፣ እና ከድምፅ አወጣጥ ትወና አንፃር የፊልሙ ጠንካራ እና ደካማ ጎኑ በመገምገም ሌሎች ፊልሞች ሲሰሩ ትወናው ላይ እንዴት መስራት እነዳለባቸው በማወቅ እክፍተታቸው በመሙላት የፊልም ትወና ኢንዱስትሪው ከፍ እንዲል ካላት ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡

## 1.2 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

•ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር ሲተነተን ምን ይመስላል ?

•ስንብት ፊልም ላይ ያሉ ተዋናዮች የፊልሙን ትወና በሚገባ ተውነውታል ወይ ?

•የስንብት ፊልም ትወና ጥሩ እና ደካማ ጎኑ ምንድነው?

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ

•የዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ዋና አላማዉ «ስንብት» ፊልም ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር ትንታኔ መስጠት ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

• ስለ ፊልም ትወና ምንነት ማሳወቅ ።

• ስንብትን ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት አንፃር መተንተን እና ማሳወቅ ።

• በፊልም ዉስጥ የነበሩት የትወና ጉድለቶች በመለየት ከዚህ በኋላ ለሚዘጋጁ ፊልሞች ጥቆማ መስጠት ።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

•ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ተመስጦ፣ዉስጣዊ ፍቺ፣ስሜት፣ማስተዋልእና ከድምፅ አወጣጥ ትወና አንፃር እንዴት እንደተተወነ ግንዛቤ ይሰጣል ፡፡

• ከዚህ በኋላ ለሚሰሩ ፊልሞች በትወና ላይ ለሚስተዋሉ ደካማ ጎኖችን እንደ ጉድለት ጠንካራ ጎንን ደግሞ እንደ ትምህርት እንዲወስዱት ።

•የዚህን አይነት ተመሳሳይ ካላቸው ጥናታዊ ፁሁፍ ለሚሰሩ አጥኝዎች እንደመረጃ ያገለግላል ።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

⁕ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ ትኩረት የሚያደርገዉ ‹ስንብት › ፊልም ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር መገምገም ላይ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

አጥኝዋ ይህ የጥናታዊ ፁሁፍ ስትሰራ ገላጭ የምርምር ስልትን መሰረት አድርጋ ሰርታለች ። ምክንያቱም በፊልሙ ዉስጥ የታዩት ትወና መልካም እና ደካማ ጎኖች ልንገልፃቸዉ ወይም ልናነሳቸዉ የምንችለዉ በማብራራት እና ምክንያታዊ በሆነ ገለፃ ነዉ። አጥኝዋ ይህን የጥናት ዘዴ መሰረት በማድረግ ከጥናቱ ጋር የሚዛመድ ጥናታዊ ፅሁፎች በማንበብ ፣ከጥናቱ ጋር የሚዛመድ መፅሀፎች በማንበብ ፣ከድህረ ገፅ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በማሰባሰብ እና ስንብት ፊልም ደጋግማ በማየት ጥናቱ ተሰርቷል ።

## 1.7 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ ጥናቱ ዳራ ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አላማ ፣የጥናቱጠቀሜታ ፣የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ አወቃቀር እና በጥናቱ ወቅት ያገጠሙ ችግሮች የያዘ ነዉ ። በምዕራፍ ሁለት የንድፍ ሃሳብ ቅኝት እና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት የያዘ ነው፡፡ በምዕራፍ ሶስት ስር ደግሞ የስንብት የፊልሙ ታሪክ ፣ ስንብት ፊልም ከተመስጦ አንፃር ፣ ከውስጣዊ ፍቺ አንፃር ፣ ከስሜት አንፃር ፣ ከማስተዋል አንፃር እና ድምፅ ከወጣጥ ትወና አንፃር ምን እንደሚመስል የመረጃ ትንተና የሚተነተንበት ሲሆን በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ፣ የመፍትሄ ሀሳቦች እና ዋቢ ፅሁፎች ያጠቃልላል ።

## 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

⁕ በቂ የሆነ ተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ማግኝት አለመቻል እና የጊዜ እጥረት ማነስ ቢሆንም እነዚህ ችግሮች በመቋቋም ጥናቱ በተሳካ ሁኔታ በተገኘዉ የመረጃ ምንጭ መሰረት ጥናታዊ ፁሁፉ መስራት ችላለች።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የንድፍ ሃሳብ ቅኝት

### 2.1 ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት

በ2013 ዓ.ም በነብዩ ማሞ ወልዲያ የኒቨርሲቲ የተሰራ ‹ተፈጣሪ እና 79 › ፊልሞች ከፊልም ትወና ጥበብ አንፃር የተሰኘው ጥናታዊ ፁሁፍ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ ከስንብት የአማርኛ ፊልም ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር የሚያመሳስላቸው ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች ከፊልም ትወና አንፃረ መዳሰሳቸው ፣ በአራት ምዕራፎች መከፋፈላቸው እና በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተናው ላይ ለፊልም ትወና አስፈላጊ ከሆኑ መስፈርቶች ከተመስጦ፣ ከዉስጣዊ ፍቺ ፣ከስሜት፣ከማስተዋል፣ ከድምፅ አወጣጥ ትወና አፃፃፍ መተንተናቸው አንድ ሲያደርጋቸው ልዩነታቸው ደግሞ "ተፈጣሪ እና ሰባ ዘጠኝ " ፊልሞች ከፊልሞች ትወና ጥበብ አንፃር የተሰኝ ጥናታዊ ፁሁፍ በሁለት ፊልሞች ላይ የተጠና ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተናው ላይ " ተፈጣሪ እና ሰባ ዘጠኝ " ፊልም ከገፅ ባህሪ እና ከግል ባህሪ አሳሳል አንፃር የሚተነትናቸው ሲሆን ስንብት ጥናታዊፅሁፍ ደግሞ በአንድ ፊልም ላይ የሚጠነጥን ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተናዉ ላይ ስንብት ፊልም ገፅ- ባህሪ እና ገለ -ባህሪ አንፃር አለመተንተኑ ይለያቸዋል።

በ2013 ዓ.ም በብርትኳን አሻግሬ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ " ከደመና በላይ " የአማርኛ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አንፃር የተሰኘው ጥናታዊ ፅሁፍ የተሰራ ነው ፡፡ ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ ከስንብት ጥናታዊ ፁሁፍ ጋር የሚያመስስላቸው ሁለቱም ጥናታዊ ፁሁፎች በፊልም ዙርያ ማተኮራቸው እና በአራት ምዕራፍ መከፋፈላቸው አንድ ሲያደርጋቸው ልዩነታቸው ደግሞ " ከደመና በላይ " ፊልም ከዝግጅት አላባዊያን ማለትም ከሙዚቃ ፣ ከግብአተ ድምፅ፣ ከብርሃን አጠቃቀም ከምስል ቅንብር ፣ ከምስል ቀረፃ ፣ ከሲኒማቶግራፊ አንፃር አጠቃሎ የሚተነትን ሲሆን ስንብት ፊልም ደግሞ ከፊልም ትወና ባህሪያት አንፃር ያተኮረ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡

## 2.2 የፊልም ምንነት

ፊልም በካሜራ አማካኝነት ምስልን አከታትሎ የገሀዱ እዉነታ የሚያስለን የኪነጥበብ ዘርፍ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ አኗኗር ፡ሀይማኖት ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ፡ታሪካዊ ክስተቶችን ወይም ክንዉኖች እዲሁም የዕለተ ዕለት የኑሮ ሁኔታዎችን እና ገጠመኞችን ወዘተ በተቀሳቃሽ ምስል አማካኝነት ለተመልካች የሚያሳይ ልዩ ጥበብ ነዉ ፡፡ ይህንን ሀሳብ የሚያጠና ክርልን የጳዉሎስ አእምሮ "የፊልም ጥበብ አዘገጃጀት ዘዴ " የተሰኘዉ መጸሀፍ ላይ እንዲህ ገልጾታል ፡-"የእይታ ጥበበ የሆነዉ ፊልም የተለያዩ ምስሎችን በተቀሳቃሽ ኪነ- ጥበብ ዘርፍ ነዉ ፡፡ ይህ ኪነ ጥበብ ዘርፍ በዉስጡም ምስልን ፣ድምጽን፣ ተግባራዊን እንቅስቃሴዎችን በማቀነባበር የእይታን ምትሀት በግበአት አማካኝነት እንቅሳቃሴ ልክ በገሀዱ አለም

የምናየዉድርጊትይመስላል፡፡"(2010፡9)ከላይእንደተገለፀውፊልምታሪክንበምስል፣በድርጊት፣በድምፅና፣እንቅስቃሴ

ቅንብር የመግለፅና የመንገር ነዉ፡፡ ፊልም ምስል ቅንብር ብቻ አይደለም ፡፡ የፊልሙ ታሪክ የሚያደምቅልን ወይም ተወዳጅ ፊልም እንዲሆንልን በውስጡ ሰው ሰራሽ ትዕይንቱ የሚያግዙ የሚደግፍ አልባሳት፣ መብራት ፣ገፀቅብ፣ሙዚቃ አርትኦት ፣ ግብአተ ድምፅ ፣ምስል ቅንብር አካቶ የያዘ ሲሆን ከነዚህ ዝግጅት አለባውያን አንዱ ትወና ነው፡፡

### 2.2.1 የፊልም ትወና አመጣጥ

የፊልም ትወና የተጀመረዉ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1895 ላያ በሉመር ወንድማቾች አማካኝነት የመጀመሪያ ጊዜ አንድ ደቂቃ ፊልም የተሰራ ሲሆን ትይንቶቹ የፈረንሳይ ዋና ከተማ በሆነችው ፓሪስ ከባቡር መውጣት እና ከሉመንድ ፋብሪካ የሚወጡ ሰራተኞች የሚያሳይ ነበር፡፡ታዲያ የፊልም ከ125 አመት ባይዘልም ግን አሁን ላይ እጀግ ተወዳጅ እና ተቀባይነቱ እየጨመረ የመጣ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ፊልም የእይታ ጥበብ ነው ታዲያ በእይታ ውስጥ ታሪክን፣ገጽ-ባህሪን፣ መቼት...የመግለጽ ትልቅ አቅም አለው፡፡

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከክርስቶስ ልደት በፊት 335 ላይ ቴስፒስ በዐለም ደረጃ የመጀመሪያው ተዋናይ ሲሆን፤ለወይን አምላክ ለሆነው ዲያኖሲስ ክብረ በአል ላይ ኮረሶች ጋ በመሆን ነበር በትረካ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወነው፡፡ ለፊልም፣ለራዲዮ ዘውጎች ለትውና ጥበብ መሰረት የሆነው የቴአትር ትወና ጥበብ ነው፡፡ በ1912 እ.አ.አ በመድረክ ትወና ታዋቂ የነበረችዉ ሳራ በርን ሀንድ በ"ካዉቦይ"ላይ ብራንኮ ቦሊ አንደርሰን እና ካኮመዲንጀብኒ ጋር በመሆን "ኲዊን ኤልሳቤት" የተሰኘዉ ፊልም ላይ በመተወን የመጀመሪያዎቹ ኮኮብ የፊልም ተዋናዮች እንደሆኑም ይነገራል ፡፡ በዚህ ወቅትም ነበር ፊቱ አርብክል እና ቻርሊ ቻፕሊን ወደ ፊልም አለም የተቀላቀሉት እነዚህ ተዋናዮች በወቅቱ የሚተዉኑት በድርጊት እና በእንቅስቃሴ ነበር የሚተዉኑት ።

በ21ኛ ክፍለ ዘመን ሞያዉ እጅግ ወደ ተወሳሰበ የኮምፒዩተር ዘመን ላይ የደረሰ ቢሆንም በአንጻሩም ወደ ሀገራችን በተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ እጅጉ ወደሀላ የቀረ የፊልም ደረጃ ባይሆንም መካከለኛ የሆነ ደረጃን የሚሆን ትወናን እናቴክኖሎጂ በመጠቀም ይሰሩ ነበር ፡፡ በአሁጉራችን ጥሩ የሚባል ትወና ባይኖርም ጥሩ ላይ ለመድረስ እየተፍጨረጨረች ትገኛለች፡፡ ሰለሞን መኮነን" የፊልም ጥበብ ገበታ"በሚለው መፅሐፍ ላይ የኢትዮጲያ የፊልም ታሪክ አጀማመር በዚህ መልኩ አስቀምጧል፡-

ፊልም በኢትዮጲያ የተጀመረው በአፄምኒልክ ዘመን ሲሆን በኢትዮጲያለመጀመሪያ ጊዜ

የተሰራው ፊልም «ሂሩትአባቷ ማነዉ ? >> የሚል ነዉ ። ለመጀመርያ ጊዜ ተንቀሳቃሽ

ምስል የታየው በአፄ ሚኒሊክ ዘመን ነው ፡፡ የኢትዩጲያ የፊልም ታሪክ በሶስት ዘመን

የተከፋፈለ ነው ። የመጀመሪያ ፈልም ዘመን ከ1950-1980 ዋችነው ።ሁለተኛዉ የ ፊልም

ዘመንከ1980-1995ዓ.ም፡፡የሶስተኛፈልምታሪክ1995እስከ አሁን ያለው ዘመንነው፡፡ (2007፡4)

ከላይ እንደተገፀው የፊልም ታሪክ በዚህ ዘመን ብዙ ስራዎች ተስርተዎል ፡፡ ከላይ እንደተገለፀዉ በሀገራችን ኢትዮጲያ ፊልም የተጀመረዉ በንጉስ ሚኒሊክ ዘመን ሲሆን ጣልያኖች የራሳቸው ዝና እና ባህል እንደማሳየት ተጠቅመውበታል ፡፡በወቅቱ የውጭ ሀገር ፊልሞች ነበር የሚታየው በኢትዮጲያ የመጀመርያ ጊዜ "ሂሩት አባቷ ማነው"?በሚል ርዕስ ተሰራ፡፡ ከዛም" አስቴር" ለእይታ በቃ ፡፡ በ1956 ሜሼልፓፓላሲ የተባለው ሰው በአባታቸው ግሪካዊ ዜግነት ባላቸው አዘጋጅ «ጉማ»የተባለዉ የመጀመሪያ የቀለም ፊልም ለእይታ በቃ። እንዲህ እንዲህ እያለ ለፊልም ትወና እድገት አመቺ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችንም በዚሁ ዘመን እየታየይገኛል ፡፡ በአጠቃላይ የፊልም ትወና የፎቶ ግራፍ እና የትያትርን መፈጠር ተከትሎ የመጣ የስነ_ጥበብ ዘርፍ ከ3D አልፎ በ7D እየተሰራ ይገኛል ፡፡

## 2 .3 የትወና ምንነት

ትወና ከፊልም ዝግጅት አላባዊያን አንድ ነው ።ትወና በድርሰት ወይም በወረቀት ላይ ተጽፎ ያለማንነት በመላበስ ለተመልካች የሚቀርብበት መንገድ ሲሆን ሰዎች የራሳቸዉን ማንነት በመተዉ ገጸ ባህሪዉን በመላበስ ሆነም ወይም መስለዉ መተወን ማለት ነዉ ፡፡ ዘላለም ተፈሪ "የፊልም ትወና ጥበብ "በሚለዉ መፅሀፍ ላይ ስለ ትወና እደሚከተለዉ ገልጾታል ፡-

ትወና ሙያ ነዉ ፡፡ ሰዎች በቲያትር ፣ በቴሌቬዥን ፣በፊልም ፣በሬዲዩ እና

በምስል የተለያዩ ታሪክን በሚተርኩ የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች በደራሲያን

ምናብ የተቀረጸ ገጸ -ባህሪያትን በመሆን የተጻፈ (ያልተፈጸመ ሊሆን ይችላል፡፡)

ታሪክን በምስል ፣በእንቅስቃሴ ፣በንግግር ፣በዘፈን ፣በድርጊት ወዘተ

ለተደራሲያን የሚተረኩበት ኪነ- ጥበባዊሙያ ነዉ፡፡ (2010፡35)

ከላይ እደተጠቀሰዉ ትወና የመሆን እና የመምሰል ብቃት የሚጠይቅ ሲሆን ተዋናዮቹ የገጸ-ባህሪዉ አካላዊ ፣ማህበራዊ ፣ስነ- ልቦናዊ እና ስነ-ምግባራዊ የገጸ ባህሪያት አሳሳል በጥልቀት በመገንዘብ መስሎ ወይም ሆኖ ገጸ-ባህሪዉን መተወን ይጠበቅባቸዋል ፡፡ እንዲሁም ትወና የማስመሰል ጥበብ እደመሆኑም መጠን መጀመሪያ ተዋናዩ ስለ ገረ -ህሪዉ በሚገባ ማወቅ እና የተሰጠዉን ገጸ- ባህሪ እሰራለዉ ብሎ እራሱን ሊያሳምን ይገባል ፡፡ በአጠቃላይ ትወና ማለት በድርሰት ወይም በቀወረቀት ተጽፎ የለ ታሪክ ተወናዮቹ የሴት ወይም የወድ አሮጊት ፣ወጣት ፣ህጻን --- ወዘተ የመሳሰሉትን ገጸ -ባህሪ ዉን በመላበስ በትያትር ፣በፊልም ፣በሬዲዩ ፣በቴሌቭዥነን ሲተወኑ የምናቃቸዉ ጥበብ ነዉ ፡፡

## 2.4 የተዋናይ ምንነት

ተዋናይ ማለት የትወና ባለሙያ ሰው ሲሆን በአንድ ድርሰት ውስጥ ያለ ገፀ-ባህሪ ወክሎ ስሜት ድምፅ እንቅስቃሴ የተለያየ ድርጊቶችን በደንብ ተላብሶ ሆኖ ወይም መስሎ የሚተወን የትወና ባለሙያሰዉ ነው፡፡በአዘጋጅ ሳሙኤል ተስፋዬ«የትወና ጥበብ »በሚለው መፅሀፍ ላይ ስለተዋናይ ትርጉም እንዲህ ገልፆታል ፡- "ተዋናይ ማለት በፅሁፍ ተውኔቱ የተፈጠሩ ምናብአለም ፍጡራንን ወክሎ በአካሉ፣በአንደበቱ ክፍሎች እናበአእምሮ ተጠቅሞ በመድረክ ላይ ግዙፍ እንደነሱ የሚያደር ክሎት ፣እውቀትና ስልጠና ያለው ጥበብ ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወትሙያተኛ ሰው ነው፡፡" (2010፡49) በዚህ ትንታኔ እንደምንረዳው ትወና ተዋናይ በስራ አካላቱ በአዕምሮና በአንደበት ክፍሎቹ ሁሉ ተጠቅሞ የህይወት ልምድ ከተፈጥሮ የተቀበለው በህይወት እና በሰዉ የቀዳውን መልሶ ለሰው ልጅ በአስገራሚ ክሎት ሚያሳይ ጥበብ ነው።

እንዲሁም ደራሲው በሳለው ገፅ-ባህሪ የተለያዩ የስሜት ለውጦች ፣አካል እንቅስቃሴ ፣የተለያዩ ድምፆችን አስመስሎ ተላብሶ የሚተወን የትወና ባለሙያ ሰው ነው፡፡ በሌላ በኩል ወሰንየለህ ጥላሁን"የፊልም ጥበብ ቅኝት " በሚለው መፅሃፍ ላይ ስለተዋናይ እንዲህ ገልፆታል ፡- "አንድ ፊልም ለማየት ከመወሰናችን በፊት የምናነሳዉ የመጀመሪያ ጥያቄ አዘጋጁ ወይም ሲኒማቶግራፊዉ ማነው? የሚለዉ አይደለም ፡፡እነማን ይሰሩበታል ? ነው የምንለው፡፡" (2005፡270) ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ተዋናዮቹ የተሰጣቸው ገፀ-ባህሪ በ ደንብ ተላብሰው ሲተውኑ ተመልካች ዘንድ ተቀባይነት እንዳላቸው እንዲሁም ጥሩ አድርገው ማይተውኑ ተዋናዮች ተመልካች ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው ያሳያል ፡፡ስለዚህ ተዋናዮቹ በትወናቸው የተመልቻች ቀልብ በመያዝ በደንብ መተወን እንዳለባቸው እና የተሰጣቸውን ገፀ- ባህሪ በደንብ ተላብሰው መተወን ይጠበቅባቸዋል ፡፡

## 2.5 የፊልም ትወና

የፊልም ትወና ተፅፎ የተቀመጠን ታሪክ ህይወትን ሰጥቶ ድርጊት፣ እንቅስቃሴ እና ድምፅን በመጠቀም ሚሰራ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡በሚተወንበት ሰዐት በተወሰነልን ስፍራ ቆመን ፣ ተቀምጠን ፣እተራመድን እና ተለያዩ ስልት ለተመልካች ማሳየት ብቻ ሳይሆን ምናደርገውን ድርጊት በመናገርም ምናስተላልፍበት መንገደው ነው ፡፡ አንድ ተዋናይ በፊልም ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋራ እራሱን ማሳደግ እና መግባባት ይኖርበታል፡፡ዘላለም ተፈሪ « የፊልም ትወና ጥበብ» በሚለዉ መጽሀፉ ዉስጥ ስለ ፊልም ትወና እንደሚከተለዉ አስፍሯል ። «የፊልም ትወና ጥበብ በሰዉ ልጅ መካከል የሚደረግ የተግባቦት ሂደት ላይ የሚመሰረት የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነዉ፡፡( 2010 ፣35 ) ይህም ማለት የፊልም ትወና ሰው ከሰው ጋራ የመግባቢያ ዘዴ ነው፡፡ማለትም አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋራ ለመግባባት የሌላውን ግለሰብ ስሜት፣ የንግግሩ ይዘት፣ ድምጽ አወጣጡ፣ የሰውነት እንቅስቃሴው፣ የፊቱ ላይ የሚነበበው ስሜት... ተጨምሮ ግለሰቡ ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል፡፡ስለዚህ የፊልም ትወና ተዋናዩ ለተመልካቹ የሚያሳየው የተግባቦት ደረጃ ላይ ይመሰረታል፡፡

አንድ ተዋናይ ገፀ-ባህሪ ወክሎ ለመተወን በሚነሳበት ሰዓት የሚተዉንበት ታሪክ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ አምኖ አስተሳሰብ፣ የኑሮ ደረጃ ፣ማንነት ልምምድና የመሳሰሉ በደንብ ማጥናት ለፊልም ትውና ዋናዉ እና አስፈለጊው ነገር ነው፡፡ የፊልም ትወና በትኩረት የሚሰራ በመሆኑ አንድ የፊልም ተዋናይ ብዙ ማንበብና መማር ይጠበቅበታል። እንዲሁም የፊልም ትወና ትኩረት ሰጥቶ በደንብ መስራት አለበት። በአካል ፣በቀለም ፣በግብር፣በምግባር፣ በስም፣ በአድራሻ፣ እና በመሳሰሉት አንድ ሰው መገለጫና መታወቂያ መለይተን የምናቃቻው ም በትወና በመሆኑ ለፊልም ትወና ትኩረት ሰጥተን በደንብ

መስራት አለብን። አንድ ተማሪ ለመማር መሟላት ያለበት ደብተር፣ እስክሪብቶ ............፣ወዘተ እንሚያስፈልገው ሁሉ ተዋናዮችም በመድረክ በፊልም እና በሬድዮ በሚተውኑበት ጊዜ ስሜት፣ተመስጦ፣ማስተዋል፣ ድምፅ ፣ ውስጣዊ ፊቺ አስፈላጊ መሳሪያዎች ናቸዉ። ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ለፊልም ትወና አስፈላጊው የሆኑትን ዋና ዋና መስፈርቶች እንዲህ ታስቃኛለች።

### 2.5.1 ተመስጦ

መመሰጥ ማለት ሃሳብህን አንድ ቦታ ላይ ሙሉ በሙሉ ስብዕና ማቆት ማለትነዉ። ይህ ማለት አንድ ሰው በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ሲሰራ ለዛስራው ትኩረት ሰጥቶ ሙሉ በሙሉ በስራው ላይ በመመሰጥ ሲሰራ የሚሰራው ስራ ስኬታማ ሲሆን እና የተሳካ ስራ ሲሰራ ነው በተመስጦ ተሰራ የምንለው። አንድ ጀርሚ ኮሚ "the art of film acting " በሚለው መፅሃፍ ላይ ስለተመስጦ እንዲህ ሲል ገልፆታል "የተመስጦ ጥበብ ትኩረት የሚያደርግዉ በተዋናዩ ሃሳብ ላይ ሲሆን ነገር ግን ግለሰቡ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላኛው ተዋንያን ስሜት ላይ መሆን ይኖርበታል "(2002፡30) (1)ከላይ እንደተገለፀዉ ተመስጦ በተዋናዩ ስሜት ላይብቻ ሳይሆን በሌላኛው ተዋንያን ምላሽ ላይ ይኖርበታል ፡፡እንዲሁም ብዙ ጊዜ በትወና የሰለጠኑ እውቀት ያላቸው ተዋናዮች በሚተወንበት ጊዜ በሚጫወቱት ገፀ-ባህሪ ታሪክ ውስጥ ለመመሰጥና ከገፅ ባህሪ ሳይወጡ መቆየት ለመተወን አይቸገሩም፡፡ ጀማሪ ተዋናይ ግን ከገፀባህሪው ጋር ከመመሰጥ ይልቅ በስራቸው ፈርሀት ውስጥ ሲቸገሩ ይታያል ፡፡ለምሳሌ ስሰራ ሰዎች ምን ይሉኛል ? ቃለ ተዉኔቱ ቢጠፋብኝስ በሚሉ ምክንያቶች ከመመሰጥ ይወጣሉ፡፡ስለዚህ አንድ ተዋናይ የተመልካችን ቀልብ ገዝቶ ሊይዝ ፣ሊያሰምን የሚችለው እርሱ ሲመሰጥ ብቻ ነው፡፡

### 2.5.2 ዉስጣዊ ፍቺ

ውስጣዊ ፍቺ ማለት አንድን ቃል ቀጥታ ከመተርጎም እና አንደበታዊ ፍቺ ምን እንደሆነ ከማወቅ በፊት ቀጥተኛፍቺ ለይተን ካወቅን በኋላ ከፋፍሎ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በእንቅስቃሴ እና በድርጊት መግለፅ ማለት ነው፡፡ዘላለም ተፈሪ" የፊልም ትወና ጥበብ" በሚለው መፅሃፍ ውስጥ ስለ ውስጣዊ ፍቺ እንደሚከተለው አሰፍሯል፡፡ "በፊልም ዉስጥ ዉስጣዊ ፍች የምንለዉ በስሜት አማካኝነት የሚከወን ንግግር የታጀበ ወይም ድመፅ አልባ ተግባቦት ነዉ ፡፡"(2010፡117) በአጠቃላይ ዉስጣዊ ፍችን ማለት በፊት ገጽታ፣ በሰዉነት እንቅስቃሴ እና በአካላችን በምናሳያቸዉ ገጽታዎች ይገልጻሉ ፡፡ ሌላዉም ማንኛዉም ቃላት ሊሆን ይችላል በሚናገሩበት ጊዜ ተመልካች ታሪኩ እዲገባዉ እና ገፀ-ባህሪ ምን ማለት እንደፈለገ ማስረዳት አለበት ፡፡ ስለዚህ አንድ ተዋናይ በሚተዉንበት ጊዜ የቃላት ዉስጣዊ ፍቺን በሚገባ ማጥናት አለበት፡፡

### 2 .5 3 ስሜት

በፊልም ላይ የመጀመርያዉ አስፈላጊ ነገር ስሜት ነዉ ምክንያቱም ካሜራዉ ከተዋናዩ ጋር ያለዉን ቁርኝነት የጠበቀ ስለሆነእያንዳንዱ ስሜት ለተመልካቹ ለመጋባት ተዋናዪ ጥሩ ስሜት ያለዉ አተዋወን ሊተዉን ይገባል ።ይህማለት ከንግግሩ ይልቅበስሜት የሚገለፁ ፀፅት፣ ማዘን መደነቅ የመሳሰሉትን ስሜቶች ከንግግር ይልቅበድርጊት እናበስሜት ቢገለፁ የበለጠ ተመልካቹ ጋርስሜቱእንዲጋባ ያደርጋል ። ስሜት በተለያዩ የሰዉነታችን ክፍሎች ሊገለፅ ይችላል በአይን የፍቅር ስሜት፣በእጅ የመጠቆም ፣ በአፍ የማሽሟጠጥ የማኩረፍ በአንገት የአሉታ እና የአዎንታ ስሜት እንጠቀምባቸዋለን ። ተዋናይ በሚተዉኑበት ሰአት ከእርሱ ጋር የሚመስራዉ ተዋናይ ስሜት ዉስጥ ሆኖ ሲሰራ እሱጋ የሚሰራዉ ስሜት ተጋርቶ የፊልሙ ታሪክ (ስሜት)በሚገባ ለማንጸባረቅ የሚረዳ ክፍል ነዉ ፡፡በዘላለም ተፈሪ "የፊልም ትወና ጥበብ "በተሰኘዉ መጸሀፍ ዉስጥ ስለ ስሜት እንዲህ ገልፆታል ፦ "ስሜት ስንል በአመለካከታችንና በአስተሳሰባችን ላይ የሚመረከዝ

በአእምሮአችን አስገዳጅነት  የሚከሰት ክስተት ነዉ፡፡" (2010፡116) ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ስሜት በልምድ ወይም በሙከራ የሚመጣ አይደለም። በአእምሮ አስገዳጅነት የሚከሰት ክስተት የሚመጣ ሲሆን አንድ የፊልም ተዋናይ የሚተዉንበት ወቅት ከእርሱጋር የሚተዉነዉ ተዋናይ ስሜት የሚደነገጥ ሲሆን  የመደንገጥ ፣የመደሰት፣የማዘን አብረዉ ተጋግዘዉ ስሜቱ ለተመልካች ማድረስ እና ተመልካችን ወደ እራሳቸዉ ስሜት ማምጣት አለባቸዉ፡፡

## 2.5.4 ማስተዋል

ማስተዋል ማለት የዉስጥን መረዳት ሲሆን ተዋናይ የተሰጠዉን ገጸ ባፀ-ባህሪ ምንነት እና ሁኔታ በማየት ወደ እራሱ ማምጣት መሞከር ማለት ነዉ ፡፡ግሩም ኤርሚያስ " መሰረታዊ ትወና" በሚለዉ መጸሀፍ ላይ ስለማስተዋል እንዲህ ገልፆታል ፡- " ምንጊዜ የምታየዉ ሰዉ ትዕይንቶች እና ድርጊቶች  ያስተዋልከዉን ነገር ለምትጫወተዉ ገፀ-ባህሪ ዉስጥ በተመልካች ህሊና ዉስጥ ግልጽና የሚታመን  ሆኖ መቅረብ አለበት ፡፡"(2008፡25 ) በዚህ መሰረት የሰዎች ባህሪን አለባበስ ፣ቅርጽ፣አበላል ---- ወዘተ ማጥናት ለፊልም ትወና በጣም ይረዳል ፡፡እንደ ተዋናይ የማስተላለፍ ችሎታ ለማዳበር ዝግጁ መሆን ሲኖርበት ስልቹ መሆን ግን የለበትም ፡፡ ስለዚህ አንድ ተዋናይ በጥልቀት አስተዉሎ መመልከት ትልቅ የሆነ ማስተዋልን ይፈጥርበታል ፡፡ስለዚህ አንድ ሰዉ በጥልቀት አስተዉሎ መመልከት ለትወናዉ ጥልቅ የሆነ ማስተዋልን ይፈጥርበታል፡፡

## 2.5.5 ድምጽ አወጣጥ

የሰዉ ልጅ እርስ በ እርስ የሚግባባዉ በቃላት እና ድምጽ በማዉጣት ነዉ። ድምጽ ለአንድ ተዋናይ መገልገያ መሳሪያ ሲሆን ተዋናዬቹ የሚናገሯቸዉ ሀሳቦች እና ንግግሮች ለተመልካች በጥራት ማስማት አለበት ፡፡ካቲሀሲ" Acting for film"በሚለዉ መፀሀፍ ዉስጥ ስለ ድመፅ አወጣጥ እንዲህ ገለፃታል ፡- " ተመልካች የተዋናዬቹን ድምጽ ጥርት ባለ መልኩ ሊያሰማ ይገባል ፡፡የተዋናዩ ድምፅ ከፍ አድርጎ ለተመልካች ማሰማት ይጠበቅበታናል ፡፡ እናም የሚያወጣዉ ድመጽ ጥርት ያለ ድምፅ መሆን አለበት ፡፡"(2003 ፡31) (2) ስለዚህ የትወና ትልቁ አላማ እና ቁም ነገር ታሪኩን ወደ ተመልካች ማድረስ ስለሆነ በፊልሙ እስከሪብት ዉስጥ ያለቀለ-ተዉኔት በስርአት ሳይቆራረጥ ለተመልካች ማድረስ ግዴታዉ ነዉ ፡፡ ስለዚህ አንድ የፊልም ተዋናይ እለት ተእለት የድምፅ ሁኔታ መጠበቅ እና መከታተል ብሎም መንከባከብ ይኖርበታ

## ምዕራፍ ሶስት

# 3. ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ባህርያት

### 3.1 የስንብት ፊልም ጭምቅ ታሪክ

የፊልሙ ታሪክ ሲጀምር የአብስራ የሚባል ከእናቱ ጋር የሚኖር ጎልማሳ መጠጥ የሚጠጣበት ገንዘብ አጥቶ ከሰዉ ቤት በመግባት ቤት ዉስጥ ብቻዋን ከምትኖር ሴት ቤት ገብቶ እየሰረቀ እያለ ታየዉ እና እራሷን ስታ ትወድቃለች።የአብስራ የወደቀችዋ ልጅ ይዞ ወደ ሆስፒታል በመዉሰድ ለማሳከም ይሞክራል። ትቷት ለመሄድ ሲያስብ ዶክተሩ የቅርብ ቤተሰብ ከጎኗ መኖር እንዳለበት ሲነግረዉ የአብስራ ዘፀአት ማንም ቤተሰብ እንደሌላት ሲያዉቅ አብራት ይቆያል። የአብስራ ከታማሚዋ ዘፀአት ጋር ይተዋወቃል እስክትድን አብሯት ይቆያል።ዘፀአትም የካንሰር ታማሚ እንደሆነች እና ለሞት ትንሽ ቀን እንደቀራት አዉቃ ወደቤት ትመለሳለች። የአብስራ ከመሞቷ በፊት ማድረግ የምትፈልገዉን ነገር ይጠይቃታል።

ዘፀአትም ከመሞቷ በፊት ያስቀየሚትን ሰዎች መሳደብ፣ያስቀየመቻቸዉ ሰዎች ይቅርታ መጠየቅ እና መዝናናት ደሰተኛ መሆን እንደምትፈልግ ነግራዉ ማድረግ የምትፈልገውን ነገር በሙሉ ከየአብስራ ጋር ታሳካዋለች።ዘፀአት ወደ ማደጎቤት በመሄድ ቅዱስ የተባለ አይኑ ማየት የማይችል ልጅ ይዛ በማምጣት እሱን ማኖርትጀምራለች።ዘፀአት ከየአብስራ እናት ጋር ትተዋወቃለች። ከየአብስራ ጋር በደንብ ይቀራረባሉ። አሁንም ድጋሜ የአብስራ ዘፀአትን ከመሞታ በፊት ማድረግ እና እንዲደረግላ የምትፈልገዉ ነገር ይጠቃታል። ዘፀአትም ከመሞቷ በፊት ማግባት፣ወይዘሮ መባል፣በምትወደዉ ሰዉ አለሟን ማየት፣መሸሽግ ዘና ማለት እንደምትፈልግ ትነግረዋለች።ዘፀአት ከግዜ ወደ ግዜ ከየአብስራ ጋር ስትቀራረብ ሁለቱም የፍቅር ስሜት ይሰማቸዋል። ዘፀአት አንዳድ ጊዜ ህፃናት ማደጎ ቤት በመሄድ ከነእርሱ ጋር ጊዜዋን ታሳልፋለች። ዘፀአት ህመሟ ብሶ ፀጉሯ የመነቃቀል ባህሪ ሲያመጣ ዶክተሩ ጋር ሂዳ ሞቷን እንዲደብቅላት ትለምነዋለች። ዘፀአት ለቅዱስ የምታረግለት እንቅስቃሴ ታቆማለች። ቅዱስ ማየት የተሳነዉ ስለሆነ ዘፀአት ድጋፏን ማቆም ትቸገራለች።

የአብስራ ህመሟ እየባሰባት እና መሞቷን ሲያስብ እየተጨነቀ ይመጣል።የአብስራ ስራ ለመፈለግ ይሞክራል። ዘፀአት እንዳይጎዳ ብላ ከሷ ማራቅ ትሞክራለች የአብስራ ግን አይርቃትም ይበልጥ ይቀራረባሉ።ዘፀአት እና የአብስራ የህፃናት ማደጎ ቤት በመሄድ የህፃናቶቹ ምኞት እና ማድረግ የሚፈልጉትን ይጠይቃሉ።ዘፀአት ቤት እያለች የሞት ስሜት ሲሰማት ወደነ የአብስራ ቤት ለመሄድ ከቤቷ ወጥታ ታክሲ ለመያዝ አቅሙ አንሷት ቁጭ ስትል የኔ ብጤዉ ሸማግሌ ሰዉየ ታክሲ አስቁሞ ያሳፍራታል ትሄዳለች።ዘፀአት ወደነ የአብስራ ቤት ስትሄድ የሰርግ ድግስ ተደግሶ ይጠብቃታል ። ቬሌዋን ለብሳ ወደ መኪና ይገባሉ።መኪናዉ ትንሽ እንደሄደ ዘፀአት በሰርጓ ቀን ትሞታለች። የአብስራም መሞቷን እነደምንም አምኖ ተቀብሎ ጠንካራ ይሆናል።ቅድስ የዘፀአት አይን ተተክሎለት አይኑ ያያል። የአብስራ የማደጎ ህፃናትን ይዞ በስራቸዉ ታዋቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር ያገናኛቸዋል ። የልጆች ምኞት ይሳካል።

### 3.1.1 የስንብት ፊልም ተዋንያን

- ፀጋነሽ ሀይሉ — እንደ ዘፀአት
- ደምዝ ጎሽሜ — እንደ የአብስራ
- ቲና ገብረአምላክ
- ዉብሸት ተክለስላሴ
- ሳሙኤል ወንድይፍራዉ

## 3.2 የፊልም ትወና

### 3.2.1 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ተመስጦ አንፃር

ስንብት ፊልም ላይ ተመስጦን በሚገባ መልኩ የተጠቀሙ ሲሆን ግን ጎልተዉ ከወጡት መካከል።

6:10-7:10ደቂቃ ላይ ዶክተሩ የዘፀአት የጤና ሁኔታ አስጊ እንደሆነ እና በህይወት የመቆየት ዕድሏ ትንሽ እንደሆነ ለየአብስራ ሲነግረዉ የአብስራ ከገባበት ተመስጦ ስሜት ወጥቶ በጭንቀት መንፈስ"ዶክተር ህመሟ ግን ምንድነዉ?"ብሎ ይጠይቀዋል ። በዚህ ትዕይንት ላይ ዶክተሩ የዘፀአት የህመም ሁኔታ አስጊ እንደሆነ ለየአብስራ ሲነግረዉ የአብስራ የዶክተሩን ንግግር በተመስጦ ሲያዳምጠዉ ቆይቶ ህመሟ ምንድነዉ ብሎ ለመጠየቅ ፊቱ ላይ በሚያሳየዉ የፍርሀት ስሜት ዶክተር ህመሟ ግን ምንድነዉ ብሎ ሲጠይቀዉ የአብስራ ከገባበት ተመስጦ ወጥቶ ሲጨነቅ ይታያል ።

14:49-16:36ደቂቃ ላይ የአብስራ ለዘፀአት ስለስራዋ ሁኔታእና ባሏት ቀሪ ጊዜ ምን ማድረግ እንደምትፈልግ ይነግራታል። ዘፀአትም በህይወት እያለች የበደሏትን እና ያስቀየሟትን ሰዎች ተሳድባ ማስቀየም እንደምትፈልግ እንዲሁም ያስቀየመቻቸውን ሰዎች ይቅርታ መጠየቅ ፣መደሰት፣መዝናና እንደምትፈልግ ስትነግረዉ የአብስራ በተመስጦ ካዳመጣት በኋላ ማድረግ የምትፈልገዉ ነገር አሁን ማድረግ ትችያለሽ ሲላት ዘፀአት ከገባችበት ተመስጦ ወጥታ ስትደሰት ይታያል።

30:58-32:34ደቂቃ ላይ የጋሽ መሀሙድ"ስንቱን አስታወስኩት" የሚለዉ የትዝታ ሙዚቃ ተከፍቶ ዘፀአት ሙዚቃዉን በተመስጦ ካዳመጠች በኋላ ሆድ በባሰ ስሜት እና በጭንቀት ስሜት "ምነዉ ሙዚቃዉ ሀዘኔን አባባሰዉ"። ትላለች።ይህም ከራሷ ጋር በአንድ ሀሳብ መመሰጧ ያሳያል።

35:32-37:34 ደቂቃ ላይ ምሽት ዝናብ እየዘነበ መኪና ዉስጥ ሁነዉ "ለምን በህይወትህ ለቀናት ብለህ እንዲሁም ለማይዘልቅ አለም ህመምን ታዉቃለህ?"ትለዋለች። የአብስራ ንግግሯን በተመስጦ ካዳመጣት በኋላ ከእርሷ ጋር የሚያሳልፈዉ እያንዳንዱ ጊዜ በቂ እንደሆነ፣በፍቅር ጥግ መኖሩ በሷ እንዳወቀ እና እሷን በማወቁ እንዳስደሰተዉ ሲነግራት ዘፀአት የደስታ ስሜት ፊቷ ላይ እየታየ በንግግሩ ስትመሰጥ ይታያል። እንዲሁም በዚህ ትዕይንት ላይ ዘፀአት ለዝናብ ያላትን ጥልቅ ፍቅር ስትገልፅ የአብስራ በተመስጦ ካዳመጣት በኋላ"እሩቅ ልብ ነዉ ያለሽ"ይላታል። ዘፀአት ይሄን ባላት ጊዜ ከገባችበት ተመስጦ ወጥታ በቀልድ ስሜት "እርግጠኛነኝ እቺ ለመጀመርያ ጊዜ ሴት ያጠመድክባት ቃል ናት" ብላ ሁለቱም ከገቡበት ተመስጦ ወጥተዉ ሲደሰቱ ይታያል ። ይህም ሌላኛዉ ተመስጦ ነዉ።

40:20-41:07 ደቂቃ ላይ የአብስራ ለዘፀአት ከመሞቷ በፊት መሆን እና ማድረግ የምትፈልገዉን ነገር ይጠይቃታል። ዘፀአትም ከስንብቷ በፊት ወይዘሮ መባል ፣ባለትዳር መባል፣የእንትና ሚስት መባል፣ከምታፈቅረዉ ሰዉ ጋር በክንዱ መሸሸግ እና አለሟን መርሳት እንደምትፈልግ ስትነግረዉ የአብስራ በተመስጦ እያዳመጣት እያለ ዘፀአት ከገባችበት ተመስጦ ድንገት ወጥታ የህፃናት ምኞት ለምን አንሰማም ብላ ሁለቱም ከገቡበት ተመስጦ ሲወጡ ይታያል።

53:38-55:59ደቂቃ ላይ ዘፀአት ለቅዱስ መፅሀፍ ላይ ስላነበበችዉ አንድ ሰዉ በአጋጣሚ ደሴት መጥቶ ይጠላቸዉ የነበረ ህዝቦች በመላመዱ እና በመዉደዱ የተነሳ ከመጣበት ሀገር መቅረቱ ለቅዱስ ታሪኩን ስትነግረዉ ቅዱስ ታሪኩን በተመስጦ እያዳመጣት እያለ ዘፀአት የሰዉየዉን ታሪክ ጨርሳ "እዉነተኛ ስንብት ከባድ ነዉ።"ብላ ከገባችበት ተመስጦ ወጥታ ስታለቅስ ይታያል። ይህም ሌላኛዉ ተመስጦ ነዉ። በአጠቃላይ ስንብት ፊልም ላይ እያንዳንዱ ትወና በሚሰራበት ጊዜ በተመስጦ ተሰርቷል።

**3.2.2 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ዉስጣዊ ፍቺ አንፃር**

በ03:35-4:22 ደቂቃ ላይ የአብስራ ዶክተሩ የዘፀአት መድሀኒት ገዝተሀአምጣ ብሎ የሰጠዉን ወረቀት ይዞ ገንዘብ ከየት አምጥቶ መድሐኒቱን እንደሚገዛዉ እያሳሰበዉ ወረቀቱን እያገላበጠ ያየዋል።በዚህ ትዕይንት ላይ የመድሀኒቱ የገንዘብ ዋጋ ብዙ እንደሆነና የመክፈል አቅሙ እንደሌለዉ በስሜቱ በድርጊቱ ያሳያል።

በ03:35- 4:22 ደቂቃ ላይዘፀአት የያብስራ እጅ ይዛ ጡቶቿ ጋር እጆቹ ታሳርፈዋለች። ውስጣዊ ፍቺ በፊት ስሜት፣በሰዉነት እንቅስቃሴ የሚገለፅ ሲሆን በዚህ ትዕይንት ላይየአብስራ የዘፀአት ጡቶቿ በእጁ ነክቶ እንደተቆረጠ ሲያዉቅ የነበረዉ የፊቱ የመደናገጥ ስሜት ይታይበታል።በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ እጆች ከዘፀአት ጡቶች ሲያርፉ ለየአብስራም ለእኛም የጡት ካንሰር ታማሚ እንደሆነች ፍንጭ ሰቶናል።

28:30-29:38 ደቂቃ ላይ የአብስራ መጠጥ  ቀርቶበት ድብርት ዉስጥ ገብቶ ለመጠጥ የሚሆን ገንዘብ አጥቶ ከእናቴ ገንዘብ ልስረቅ አልስረቅ እያለ እጁ እየተንቀጠቀጠ ከ ራሱጋር ትግል ካደረገ በኋላ ሱሱን መቋቋም አቅቶት ከእናቱ ገንዘብ ሰርቆ  ከቤት እየወጣ እያለ እናቱ ታገኘዉ እና ላንዳድ ነገር ይሁንህ ብላ ገንዘብ ትሰጠዋለች።ዉስጣዊ ፍቺ በስሜት በድርጊት የሚገለፅ ሲሆን በዚህ ትዕይንት ላይ እናቱ ገንዘብ ስትሰጠዉ  የመሳቀቁ ስሜት እንዲሁም ስሰርቅ አየችኝ አላየችኝም ብሎ ሲጠራጠር የፊቱ ስሜት ላይ በደንብ ገልፆታል። እንዲሁም ሱሱ ቀርቶበት የነበረዉ የፊቱ ስሜት መለዋወጥ እና እጁ ሲንቀጠቀጥ ላለመሰረቅ የሚያሳየዉ ድርጊቱ ሳይጠጣ ማደር ቀርቶ መዋል እንደማይችል እና ለሱሱ ሲል ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይል ያሳየናል።

32:40-33:30  ደቂቃ ላይ የአብስራ ሰክሮ መጥቶ ለእናቱ ከዚህ በፊት የሰጠችዉ ገንዘብ እና የሰረቃትን ገንዘብ  እያሳየ "ልከፍለዉ ስል መቀነትሽን መቀነትሽን አለኝ።"ይላታል። በዚህ ትዕይንት ላይ ልጇ የአብስራ የሰረቀዉ እና የሰጠችዉ ገንዘብ እያሳት ልከፍለዉ ስል መቀነትሽ መቀነትሽ አለኝ ሲላት የእናቲቱ በንግግሩ ምንያህል እንደተከፋች ፣ እንደተጎዳች ፊቷ ላይ በምታሳየዉ የማዘን እና ልብ የመሰበር ስሜት  እንዳዘነች እና እንደተከፋች  ፊቷ ላይ ስሜቱን  በደንብ ገልፃዋለች።

34:55-35:18 ደቂቃ ላይ የአብስራ ሁሌ መጠጥ ከሚጠጣበት ቤት ሂዶ በሩ ጋር ልግባ አልግባ እያለ ከራሱ ጋር ከተጋጨ በኋላ ሀሳቡን ቀይሮ ሲመለስ ይታያል። በዚህ ትዕይንቱ ላይ የአብስራ ሁሌ አልኮል ከሚጠጣበት ቤት በር ሁኖ ገብቼ መጠጥ ልጠጣ አልጠጣ እያለ ከራሱ ጋር በሚያደርገዉ ትግል እና ፊቱ ላይበሚያሳየዉ መሸማቀቅ ስሜት የአብስራ ሱሱን ለመተዉ እንዳሰበ ያሳያል።

1:00:14-1:02:21 ደቂቃ ላይ ዘፀአት ፀጉሯን ለማስያዝ እያስተካከለች እያለ ፀጉሯ ሲነቃቀል ታየዋለች። በዚህ ትዕይንት ላይ ዘፀአት ፀጉሯ ሲነቃቀል በምታይበት ጊዜ የፊቷ የመጨነቅ ፣ የመከፋት ስሜት ይታይባታል። ይህም የፀጉራ መነቃቀልእና ከፊቷ የመጨነቅ ስሜት በሽታዉ እየተባበሰ መምጣቱ ለሷም ለእኛም ፍንጭ ሰጥቶናል።

1:05:00- 1:05:34 ደቂቃ ላይ የአብስራ እናት ለዘፀአት ፀጉሯ ቅባት ቀብታ እያሸቻት"እቅፎ የማላዉቃት እናቴን እናቴን ቢያሰኘኝ ነዉ" ብላ ተናግራ ላለማልቀስ የምታደርገዉ ትግልእ ና በተናገረችዉ ቃል እናቷን እንደማታዉቃት እና እንደናፈቀቻት ከቃሏም ከስሜቷም በእናት እቅፍ ዉስጥ መታቀፍ እንደናፈቀች ያሳየናል።

1:29:26-1:30:07 ደቂቃ ላይየአብስራ ዘፀአት በሞት ከተሰናበታት በኋላ ቤት ብቻዉን ተከዞ እናቱ ታየዉ እና."አሜን በል ልጄ።ትንሳኤዋን በአንተ ታየዋለህ አትግደላት ልጄ።"ብላ ያመጣችዉን ጉልባንታቀርብለታለች። በዚህ ትዕይንት ላይ እናቲቱ ልጃ የአብስራ በዘፀአት ሞት ምክንያት ልጇ እንደዛ ተጎድቶ ማየቷ እና ዘፀአትን በመሞት ማጣቷ እያሳሰባት አይኖቿ እንባ ሲሞሉ እና በምታሳየዉ የፊቷ የመተከዝ ስሜት እንዳዘነች እንደተከፋች ያሳያል።እንዲሁም የአብስራ በሚያሳየዉ የፊቱ የማዘን ፣ ልብ የመሰበር የማልቀስ ስሜት እና በአበላሉ በጣም እንደተጎዳ ያሳያል።

### 3.2.3 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ስሜት አንፃር

00:10-00:43 ደቂቃ ላይ የአብስራ የሚጠጣዉ መጠጥ አልቆበት ነገ ገንዘቡ አምጥቶ እንደሚከፍለዉ እና ለአሁን በዱቤ እንዲሰጠዉ ይለምነዋል። አስተናጋጁ በቁጣ እና በብስጭት ውጣልኝ ብሎ ያስወጠዋል። በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ አስተናጋጁን መጠጥ በዱቤ እንዲሰጠዉ እባክህ ብሎ ሲለምነዉ የነበረ የመለመን ስሜት እና አስተናጋጁ ለአብስራ በዱቤ መጠጥ እንደማይሰጠዉ እና ከቤቱ ዉጣ እያለ ሲያስወጣዉ የነበረዉ የመቆጣት ፣የብስጭት ስሜቱ ፊቱ ላይ በሚያሳየዉ ንዴት አዘል ቁጣ እና ብስጭቱ በደንብ ገልፆታል።

00:45-1:34 ደቂቃ ላይ የአብስራ ከዘፀአት መኖርያ ቤት ገብቶ ገንዘብ እየሰረቀ እያለ ዘፀአት የአብስራን ከፊት ለፊቷ  እየሰረቀ ስታየዉ እራሷን ትወድቃለች። በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ ዘፀአት እራሷን ስታ በምትወድቅበት ጊዜ  ግራ እየተጋባ ያያታል ። በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ ዘፀአት ራሷን ስታ በምትወድቅበት ጊዜ በተጨነቀ ፣ ግራ በተጋባ እና በፍርሀት  ስሜት ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ የመጋባት ፣ የመጨነቅ  እና የመፍራት ስሜቱ ጥሩ ሆኖ እያለ ከዚህ በላይ ስሜቱን መስራት ይችል ነበር።እንዲሁም ዘፀአት የአብስራን በምታይበት ጊዜ ያሳየችዉ የፊቷ የመደናገጥ ፣የፍርሀት ስሜት እና ስታየዉ የምታወጣዉ የድንጋጤ ጩሆት ድምፅ በተገቢ መልኩ ተሰርቷል።

3:05-3:29 ደቂቃ ላይ የአብስራ እናት ልጇ የአብስራ አለመምጣቱ አሳስቧት ስልክ ስትደዉልለት የአብስራ ስልኩ ይዘጋባታል። በዚህ ትዕይንት ላይ የእናቲቱ የልጇ አለመምጣት እና ስልክ አለማንሳቱ የመጨነቅ ስሜቷ እና የአብስራ ዘፅአት አንዳች ነገር እንዳትሆን ሰግቶ የመጨነቅ ስሜት ሁለቱም ጋር የመጨነቅ ስሜታቸዉ በፊት ገፃቸዉ ስሜቱን በደንብ ገልፀዉታል።

03:35-4:54 ደቂቃ ላይ የአብስራ ለዘፀአት መድህኒት ገዝተህ አምጣ ተብሎ የተሰጠዉ ወረቀት ይዞ እያየ ከተጨነቀ በኋላ ገንዘቡ ከየትም እንደሚያመጣው አዉቆ ሀሳቡን ቀይሮ ለዶክተሯ አይየለከተኝም ብሎ ከዶክተሯ ጋር ከተጋጨ በኋላ ዘፀአትን ሲያያት ከንዴቱ ስሜት በረድ ይላል። በዚህ ትዕይንት ለዘፀአት መድህኒት ገዝተህ አምጣ ተብሎ ገንዘቡን የት እንደማያመጠዉ እያሳሰበዉ ወረቀቱን ይዞ የሚጨነቀዉ ስሜት፣ በብስጭት እና በንዴት ስሜት ዶክተሯን አይመለከተኝም ያላ ስሜት እና ዘፀአትን ሲያያት ከቁጣ መንፈሱ ሲረጋጋ ይታያል። የተለያዩ የስሜት ለዉጦችን  በመጠቀም በተገቢ ሆኔታ ተሰርቷል።

14:03-14:48 ደቂቃ ላይ ከቤቷ ፊትለፊት የሚኖረዉ ጎዳና ተዳዳሪዉ የኔቢጤ ሽማግሌ ሰዉየ ዘፀአት ተሽሏት ከህክምና ስትወጣ ሲያያት የነበረዉ የመከፋት ስሜት እና ደህና እንደሆነች ስትነግረዉ የነበረዉ የደስታ ስሜት ጥሩ ሁኖ እያለ ከዚህ በላይ ስሜቱን ማሳየት ይችል ነበር።

18:02-18:30 ደቂቃ ላይ አንድ ወጣት ልጅ ጋር ሂዶ እርጉዝ እንደሆነች እና ምግብ እንዳማራት ነግሮት ከወጣቱ ጋር ዘፀአት እና የአብስራ አብረዉ በልተዉ እየመሰገነችዉ እያለ ያረገዘችዉ ልጅ የዉሸት መሆኑን ሲያዉቅ በእጁ እያማተበ የሚያሳየዉ የግንጋጤ ስሜት ብዙ ስሜት የሚሰጥ አይደለም ። ምክንያት ልጁ የዉሸት መሆኑን ሲያዉቅ ፊቱ ላይ የሚያሳየዉ የድንጋጤ ስሜት ላይ ፊቱ ላይ ፈገግታ ይታይበት ነበር እናም ይህ ተገቢ የሆነ ስሜት አይደለም ።

1:01:23-1:04:15 ላይ ቅዱስ ዘፀአት ልብሱን አስተካክላ እንድታለብሰዉ ይጠይቃታል። ዘፀአት እንባ እየተናነቃት በእልህ እና በቁጣ ስሜት ከዚህ በኋላ ማንኛዉም ነገር ማድረግ ያለበት እሱ እንደሆነ እና በራሱ ችሎ እንዲበላ እንዲለብስ በቁጣ ተናግራዉ ከሄደች በኋላ ከንዴቷ ስሜት በረድ ብላ ምግብ ይዛ መጥታ በማባበል ስሜት እንዲህ የተናገረችዉ ጠልታዉ ሳይሆን እንዲጠነክርላት እንደሆነ ትነግረዋለች። በዚህ ትዕይንት ላይ ዘፀአት እንደዛ ስትቆጣዉ ቅድስ በሚያሳየዉ የፊት ገፅ ፍርሀት እና ልብሱን እራስህ ልበስ ብላ ተቆጥታ ሂዳ ምግቡን ስታመጣ ቅዱስ ዘፀአት መምጣቷን ሲያዉቅ  በፍርሀት ልብሱን ሲለብሰዉ የነበረዉ የፍርሀት ስሜቱ በሚያሳየዉ  የፊት ገፅ ፍርሀቱ ስሜቱ በደንብ ገልፆታል ። እንዲሁም  ዘፀአት ለቅዱስ ከዚህ በኋላ እራሱን ችሎ እንዲበላ ስትቆጣዉ የነበረ  የቁጣ ስሜቷ እና

እንደዛ የተናገረችዉ እንዲጠነክርላት እንጂ መቼም እንደማትጠላዉ ስትነግረዉ በማባበል ስሜት ነበር እና የሁለቱም ስሜት በተገቢ ሁኔታ ተሰርቷል።

1:13:11-1:14:22ላይ የአብስራ ሲጨነቅ አይታ ምን እንደሆነ ትጠይቀዋለች። የአብስራም ተስፋ በቆረጠ በሀዘን ስሜት ዘፀአት ትታዉ እንደምትሄድ እና ያለእሷ መኖር እንደማይችል ይነግራታል። እናቲቱም የልጇ መከፋት አስተዉላ በማፅናናት ስሜት" ህይወት ፈጣን ናት።በማናችንም ህይወት ዉስጥ ላይ ብርሀን በጨለማ ፈጥኖ መቼ እንደሚተካ አናዉቅም።"ብላ ካፅናናችዉ በኋላ ዘፀአት ከመሞቷ በፊት የምትፈልገዉን ነገር አድርግላት ትለዋለች። በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ በቅርቡ ዘፀአት እንደምትለየዉ እያሰበ ተስፋ የመቁረጡ ስሜት ጭንቀቱ ፣ሀዘኑን ፣ ሆድ የመባስ ስሜቱ በእናቲቱ ላይ ያለ የልዷ መጨነቅ እና የዘፀአት መሞት እያሳሰባት የምትጨነቀዉ የሀዘን ስሜት በሚገባ መልኩ ተሰርቷል።

1:15:38-1:17:45 ላይ ዘፀአት ለያአብስራ ከዚህ በኋላ አጠገቤ እንዳትደርስብኝ ሂድልኝ ተወኝ፣ልቀቀኝ፤ ልሂድበት፤ አታጓጓኝ ብላ በምሬት እያለቀሰች ከቤቷ ታባርረዋለች ። በዚህ ትዕይንት ላይ ዘፀአት የአብስራን ተወኝ፣ልቀቀኝ፤ ልሂድበት፤ አታጓጓኝ ብላ በምሬት እያለቀሰች ከቤቷ ካባረረችዉ በኋላ ላለማልቀስ የምታደርገዉ ጥረት እና እራሷን እያፅናናች ያለዉ ስሜት በጥሩ ስሜት ተሰርቷል ።

1:20:17-1:21:22ላይ የአብስራእናት እና ዘፀአት መንገድ እየተጓዙ ልጇ የአብስራ የሱስ አመሉ በመተዉ ፈጣሪዋን እና ዘፀአትን እያመሰገነች እንዲሁም ለሷ ማሳከሚያ ገንዘብ እንደሌላት እና ከልቧመርቃ ስታመሰግናት ዘፀአት ተስፋ በቆረጠ ፣በተሰላቸ ስሜት እንባ እየተናነቃት ላለማልቀስ ፣ እራሷን ለመቆጣጠር የምታደርገዉ ትግል በፊቷስሜት ሆነ በአረማመዷ ስሜቱን በሚገባ ተሰርቷል።

1:21:24-1:22:29 ላይ የአብስራ እና ዘፀአት በማደጎ ቤት የሚኖሩ ህፃናት መሆን እና ማድረግ የሚፈልጉትን ነገር ተጠይቀዉ ምኞታቸዉን በሚናገሩ ጊዜ ስሜታቸዉ ጥሩ ቢሆንም የማስመሰል ስሜት፣የፍርሀት ስሜት ይታይባቸዉ ነበር።

1:26:30-1:29:20 የአብስራ እና ዘፀአት ተጋብተዉ ወደ መኪናዉ በሚሄዱበት ጊዜ ዘፀአት በጣም እያመማት ባልታመመ መንፈስ፣የአብስራም ደስታ ባለዉ የመጨነቅ ስሜት ሁለታቸዉም በዉስጣቸዉ ይዘዉ ወደ መኪናዉ ዉስጥ ይገባሉ። በዚህ ትዕይንት ላይ ስሜታቸዉ ተገቢ ሲሆን በዚሁ ትዕይንት ላይ ዘፀአት እና የአብስራ መኪና ዉስጥ ሁነዉ ዘፀአት በታመመ እና በደከመ መንፈስ "በስቅለት ቀን ግንሰርግአይከብድም?"ትለዋለች።የአብስራም በተረጋጋ እና በጭንቀት መንፈስ "ወይዘሮ ዘፀአት ፍቅር የተገለፀዉ በስቅለት ነዉ።"ይላታል።ዘፀአት ይሄንን ባላት ጊዜ በተፅናና እና በህመም መንፈስ፣ትንፋሿ እየተቆራረጠ በጣረ ሞት መንፈስ በመድከም ስሜት "ይሁን ስለሰረከኝ አመሰግናለሁ።" ብላ ለመናገር

አቅሙ ሲያንሳት  በእጇ የመሰናበት ስሜት አሳይታ ከዚህ አለም በሞት ትለያለች፡፡በዚህ ግዜ የአብስራ ማመን በሚያቅተዉ ስሜት  ስሟን ደጋግሞ  እየጠራ መኪናዉ መንቀሳቀስ ይጀምራል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ትዕይንት ላይ ስሜት ሰጥተዉ በደንብ አድርገዉ ተዉነዉታል፡፡ ለምሳሌ የዘፀአት ብንመለከት ዘፀአት ታማ ለያአብስራ ይሁን ስለሰረከኝ አመሰግናለዉ ብላ በምትናገረዉ ጊዜ መናገር እያቃታት የምታወጣዉ የትንፋሽ መቆራረጥ ድምፅ፣ ፊቷ ላይ በምታሳየዉ የመድከም፣ የመታመም ስሜት እና የሰዉነቷ የመዛል የመድከም ስሜት እንዲሁም በሽታዉ እየባሰባት ሲመጣ ወደ ማይቀረዉ የሞት አለም ልትሄድ ስትል ለየአብስራ ቻዉ ብላ ለመናገር አቅሙ ሲያንሳት በእጇ የተሰናበተች ስሜት በጥሩ የስሜት አተዋወን የተተወነ ሲሆን በያአብስራም በኩልም ዘፀአት በሞት ካጣት በኋላ ዘፀአት ብሎ ስሟን ሲጣራ ያለዉ ትዕይንት ላይም የአብስራ  እያለቀሰ የዘፀአት ስም የሚጠራበት ድምፅ አወጣጡ ምን ያህል እንደተጎዳ ፣እንዳዘነ ያሳያል በሚያወጣዉ የለቅሶ ድምፅ እንደተጎዳ ያሳያል ፡፡እንዲሁም ፊቱ ላይ የሚታየዉ የመሰበር እና የሀዘን ስሜቱ በጣም እንደተጎዳ የሚያሳይ ሲሆን እንዲሁም መሞቷን አምኖ ተቀብሎ ላለማልቀስ የሚያደርገዉ ትግል በደንብ ተደርጎ በስሜት የተሰራ ሲሆን በዚህ ትዕይንት ላይ የሁለቱም የስሜት ምላሽ አንድም የማስመሰል ስሜት አይታይበትም፡፡ በአስገራም ስሜት ተሰርቷል፡፡

1:29::26-1:30:07 ደቂቃ ላይ የአብስራ ዘፀአትን ከተሰናበታት በኋላ ቤት ብቻዉን በሀዘን ተጎድቶ ተከዞ እናቱ በመጨነቅ ስሜት"አትግደላት የኔ ልጅ፡፡ ትንሳኤዋን ባንተ ታየዋለህ፡፡"ብላ ያመጣችዉን ጉልባን እንዲበላ ታቀርብለታለች፡፡ በዚህ ትዕይንት ላይ የእናቲቱ የሀዘን የመጨነቅ ስሜት ፡፡  ሀዘኗም ጭንቀቷም በንግግሯ እና በፊቷ ገፅ በጣም ስሜቱን በደንብ ገልፃዋለች፡፡ እንዲሁም የአብስራ ምን ያህል እንደተጎዳ፣ልቡ እንደተሰበረ፣በሚያሳየዉ የፊቱ ገፅ እና በአበላሉ የሀዘኑ ስሜት በደንብ ገልፆታል፡፡

1:30:09-1:30:27 ላይ የአብስራ ለቅዱስ የተተከለለት አይን የዘፀአት እንደሆነ ነግሮት አይንህን ግለጥ ይለዋል፡፡ቅዱስ በማኩረፍ ስሜት እያለቀሰ "አልገልጥም ማየት የፈለኩት እሷን ነዉ፡፡"ብሎ የአብስራን ተሰናብቶ እየሄደ እያለ የአብስራ ቅዱስን ጠርቶ " ዘፀአት አልሞተችም፡፡ ባንተዉስጥ አለች፡፡የተተከለለህ አይን የእሷ ነዉ፡፡ አላይም ካልክ ታዝንብሀለች፡፡ለራስህ ብለህ ሳይሆን ለሷ ስትል እይ፡፡" ይለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ቅድስ የሚያሳየዉ የደስታ ስሜት ጥሩ ሁኖ እያለ ከዚህ በላይ የደስታ ስሜቱን መስራት ይችል ነበር፡፡በአጠቃላይ በስንብት ፊልም ዉስጥ የስሜት አገላለፃቸዉ ጥሩ ሲሆን በአጃቢ ተዋናያን ግን ከስሜት የመዉጣት ችግር ይታይባቸዋል፡፡

**3.2.4 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ማስተዋል አንፃር**

01፡14-1፡40 ደቂቃ ላይ ዘፀአት የአብስራ እየሰረቀ ስታገኘዉ ጊዜ ራስን ስታ ትወድቃለች ። በዚህ ትዕይንት ላይ ዘፀአት ራሷን ስታ በምትወድቅበት ጊዜ ዘፀአት እንደታመመች የአብስራ አስተዉሏል።

2፡20-3፡03ደቂቃ ላይ ዘፀአትን ክሊኒክ ቤት አስገብቶ ልሄድ ስል ዶክተሩ ዘፀአት በጣም እንደታመመች እና የቅርብ ቤተሰብ እንደሚያስፈልጋት ይነግረዋል። የአብስራም ምን አገባኝ አይነት ስሜት ካሳየ በኋላ ተመልሶ በመምጣት "ጓደኛዋ ነኝ"በማለት ከዘፀአት ጋር ይሆናል። በዚህ ትዕይንት ላይ አብስራ ዘፀአት ላይ ባደረሰባት ነገር ዘፀአት አንድ ነገር ብትሆን እሱ እንደሚጠየቅ እና ቤተሰብ እንደሌላት ብቻውን እንደምትኖር አስተውሏል።

4፡56-5፡39 ደቂቃ ላይ የአብስራ ለዘፀአት የመድሀኒት መግዣ የሚሆን ገንዘብ ሲያጣ ከእናቱ ቤት በመሄድ የቤታቸዉ ቴሌቬዥን ለመሸጥ ይዞት ሊሄድ ሲል እናቲቱ " ብድር ካለብህ እኔ እከፍለዋለዉ " ብላ እየለመነችዉ የአብስራ ለመጠጥ እንዳልሆነ ነግሯት ቴሌቬዥኑ ይዞት ይሄዳል ።በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ የቤታቸዉን ቴሌቬዥን ተሸክሞ ይዞ በሚሄድበት ጊዜ እናቲቱ ሸጦ ለመጠጥ እንደሚያውለው እና መጠጥ በዱቤ ጠጥቶ ቴሌቬዥኑን ሸጦ ብድሩን እንደሚከፍልበት አስተውላለች።

11፡37-12፡40 ደቂቃ ላይ የአብስራ ዘፀአት የሰጠችውን ምግብ ይዞ ሂዶ ከዘፀአት ቤት ፊት ለፊት የሚኖሩ ለኔቢጤ ሽምግሌ ሰዉየ ምግቡን ይሰጧቸዋል። በዚህ ላይ ዘፀአት መልካም ሴት እንደሆነች አስተዉሏል። እንዲሁም በዚህ ትይንት ላይ የአብስራ ለየኔቢጤ ሽማግሌ ምግቡን ሰጦት ከዘፀአት ቤት ገብቶ ሲወጣ ዘፀአት አንዳች ነገር እንደሆነች አስተውሎ የአብስራን ተከትሎ ዘፀአት ወደአለችበት ህክምና ስሄድ ይታያል።በዚህ ትዕይንት የአብስራ ዘፀአት ምንያህ መልካም ሴት አስተዉሏል ።የኔ ብጤ ሽማግሌ ሰዉየዉም ዘፀአት አንድ ነገር እንደሆነች አስተዉሏል ።

በ20፡55-21፡10 ደቂቃ ላይ ዘፀአት ከነ አብስራ መኖሪያ ቤት ሂዳ ቤታቸውን በአይኖቿ ትቃኛለች። ይህም የአብስራ የሚኖረው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እንደሆነ አስተውላለች።

በ22፡35-23፡30 ደቂቃ ላይ ዶክተሩ የዘፀአትን የህመሟ ሁኔታ ከፍተኛ ደረጃ እንደደረሰ ለመናገር ሲጨነቅ እና ሲጠበብ የፊቱን ስሜት አስተውላ "መልስህን ሳትነግረኝ አውቀዋለሁ። ዶክተር ታማሚዎች ቀድመህ ጭንቅላታቸውን አክምላቸው ምክንያቱም መዳን የሚጀመረው ከዛ ነው"። ትለዋለች። በዚህ ትዕይንት ላይ ዘፀአት ዶክተሩ ፊቱ ላይ በሚያሳየዉ መጨነቅ እና ለመናገር ፈራ ተባ እያለ የሚሳየዉ የፍርሀት ስሜት ህመሟ እየባሰ መምጣቱ ዶክተሩ ፊቱ ላይ በሚያሳየዉ የመጨነቅ ስሜት ህመሟ እንደባሰ አስተውላለች።

በ52፡16-53፡25 ደቂቃ ላይ ዘፀአት በሀሳብ እንደተዋጠች አስትውሎ የዘፀአትን ፊት በእጁ እየዳበሰ "ናፈቀሽ" ይላታል። በዚህ ትእይንት ላይ ቅዱስ ዘፀአት ስለአብስራ እያሰበች እንደሆነ አስተውሏል።

በ1፡23፡58-1፡24፡42 ደቂቃ ላይ ዘፀአት በጣም ታማ እና ደክማ የበሯን በር ከፍታ ወደነ የአብስራ ቤት ለመሄድ ታክሲ አስባ ለማስቆም አቅሙ ሲያንሳት እና ህመሙ ፀንቶባት ሲያማት ቁጭ ስትል ሽማግሌው የኔቢጤ ሩጦ ሂዶ ታክሲ በማስቆም ያሳፋራታል። በዚህ ትእይንት ላይ የእኔቢጤ ሽማግሌው ሰውዬ ዘፀአት በጣም እንዳመማት እና ታክሲ እንደሚያስፈልጋት አስተውሏል። በአጠቃላይ በዚህ ፊልም ውስጥ ተዋንያኑ ስለገፀ-ባህሪው በሚገባ አጥንተዋል፤ አስተውለዋል።

**3.2.5 ስንብት ፊልም ከፊልም ትወና ድምፅ አወጣጥ አንፃር**

የፊልም ትወና እንደመድረክ ትወና ከፍተኛ ድምፅ አያስፈልገዉም ።ምክንያቱም በፊልም ትወና ላይአብዛኛዉ ጊዜ ታሪክ የምንገልፀዉ በድርጊት እና እንቅስቃሴ ነዉ ።ይህ ማለት ግን የፊልም ትወና ድምፅ አያስፈልገዉም ማለት  አይደለም ።በፊልም ትወና ላይ ስሜት ያለዉ ድምፅ  አወጣጥ ያስፈልጋል ። ይህ ማለት አንድ ተዋናይ እየተሾካሾከ ፣ በንዴት ፣ በመገረም ፣ .....ወዘተ ሲያወራ ለእያንዳንዱ ስሜት በተለያየ ድምፅ ነዉ የሚተወነዉ ማለትነዉ ።

1:07:22_1:08:13 ደቂቃ ላይ ስንመለከት የአብስራ ሰክሮ ከፈጣሪዉ ጋር ሲጋጭ ይታያል ። በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ ሰክሮ የሚያወጣዉ የስካር ድምፅ እንደሰከረ በድምፅ አወጣጡ መረዳት ይቻላል ።

1:13:11-1:14:22ላይ የአብስራ ሲጨነቅ አይታ ምን እንደሆነ ትጠይቀዋለች። የአብስራም ተስፋ በቆረጠ በሀዘን ስሜት ዘፀአት ትታዉ እንደምትሄድ እና ያለእሷ መኖር እንደማይችል ይነግራታል። እናቲቱም የልጇ መከፋት አስተዉላ በማፅናናት ስሜት" ህይወት ፈጣን ናት።በማናችንም ህይወት ዉስጥ ላይ ብርሀን በጨለማ ፈጥኖ መቼ እንደሚተካ አናዉቅም።"ብላ ታፅናናዋለች ። በዚህ ትዕይንት ላይ የአብስራ በሀዘን በለቅሶ የሚያወጣዉ ስሜት ዉስጥ ሁኖ የሚያወጣዉ ድምፅ ያለበትን የሀዘን ፣ የመከፋት ስሜት በትክክል ገልፆታል ።

00:10-00:43 ደቂቃ ላይ የአብስራ የሚጠጣዉ መጠጥ አልቆበት ነገ ገንዘቡ አምጥቶ እንደሚከፍለዉ እና ለአሁን በዱቤ እንዲሰጠዉ ይለምነዋል። አስተናጋጁ በቁጣ እና በብስጭት ውጣልኝ ብሎ ያስወጠዋል። በዚህ ትዕይንት ላይ አስተናጋጁ በየአብስራ ምክንያት ተናዶ ስለነበር በብስጭት እና በጭሆት ዉጣልኝ ብሎ ከመጠጥ ቤቱ ሲያስወጣዉ ይታያል ። ይሄዉም የድምፅ አወጣጥ ጩሆት የተቀላቀለበት ስለሆነ በትክክልምያለበትን ዉስጡ ያለዉን የምሬትየመሰልቸት እና ንዴት ስሜት ለተመልካቹ አጋብቷል ።

በዚህ ፊልም ውስጥ ላይአንዳንድ ትዕይንቶች ላይ ተዋናዮቹ የሚናገሩት ቃለ ተዉኔት ጥርት ብሎ የማይሰሙ ቦታዎች አሉ ። በተለይ በዋናገፀ ባህርያት  የአብስራ ሁኖ የሚጫወተዉ ገፀ ባህሪ ስንመለከት ሲናገር ቃለ ተዉኔት ምን ለማለት እንደፈለገ ቃላቱም ድምፅም ጥርት ብሎ የማይሰሙ ቦታወች አሉ ። ለምሳሌ

በ56:54-57:28 ደቂቃ ላይ ምሽት መጠጥ እየጠጡ"ሁሌ አስማተኛ ነኝ ትል የለ? እስኪ ዛሬ ባለህበት አቁምልኝ  ትላንትም ነገንም የለላ አድርግልኝ።ብላ ስትነግርው የአብስር ቀስ ብሎ ሲናገር ስለነበር  ምን እንደሚል ቃለ ተዉኔቱ አይሰማም ነበር ይህ  ደግሞ ስህተት ነዉ ምክንያቱም ተመልካች ፊልሙን በሚያይበት ወቅት እያንዳንዱ ቃለ ተዉኔት ማሰማት አለበት እና መረዳት ስላለበት ነዉ ።

በ59:23-59:48 ደቂቃ ላይ ከዘፀአት ምኝታ ክፍል ሆነው"ለምንድነዉ ግን የጠየኩህን ሁሉ እሺ የምትለኝ ስለማሳዝንህ ነዉ?"ብላ ስትጠይቀው  የአብስራ የሚናገረዉ ቃለ ተዉኔት  ጥርት ብሎ አይሰማም ነበር ይህም ፊልሙ ደካማ ጎኑ መሆኑ ያሳየናል ።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች

### 4.1 ማጠቃለያ

ትወና በድርሰት ወይም በወረቀት ላይ ተፅፎ ያለ ማንነት ወርሰን ለተመልካች የምናቀርብበት መንገድ ሲሆን ሰዎች የራሳቸዉን ማንነት ለሳዕታት ትተዉ የሌላዉን ማንነት ወርሰዉ መስራት ማለት ነዉ።ከዚህም ጋር ተያይዞ ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በሀገራችን ያለ የፊልም ጥበብ ትወናንበስንብት ፊልም ተመልክቶ የፊልም ትወና በጥልቀት የዳሰሰ ሲሆን የፊልም ምንነት፣የትወና ምንነት፡የትወና ታሪካዊ ዳራ ፣የፊልም ትወና አጀማመር፣የተዋናይ ምንነት፣የፊልም ትወና ምንነት እና ለፊልም ትወና አስፈላጊ የምንላቸዉ መስፈርቶች ተመስጦ፣ዉስጣዊ ፍቺ፣ስሜት፣ማስተዋል እና ድምፅ አወጣጥ ምን እንደሚመስል ጠጥልቀት ደስሷል። በዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ ስንብት ፊልም ከተመስጦ አንፃር፣ዉስጣዊ ፍቺ አንፃር፣ስሜት አንፃር፣ማስተዋል እና ድምፅአወጣጥ አንፃር ትወናዉ ምን እንደሚመስል በጥልቀት የዳሰሰ ሲሆን በፊልሙ ያለ ትወና ለመዳሰስ በተምከረዉ መሰረት የፊልሙ ትወና ጠንካራ እና ደካማ ጎኑ ለማየት ተችሏል። ስንብት ፊልም ላይ የተወኑት ዋና ገፀ ባህርያት በፊልሙ ዉስጥ በሚገባ መልኩ የፊልሙን ታሪክ እንደገለፁት በምዕራፍ ሶስት ላይ በምዕራፍ ሁለት በተገፁት በተመስጦ፣ዉስጣዊ ፍቺ፣ስሜት፣ ማስተዋል እና ድምፅ አወጣጥ ትወና አንፃር በእነዚህ የፊልም ትወና መስፈርቶች መሰረት ስንብት ፊልም ተገምግሟል። ታድያ ስንብት ፊልም ላይ አጥኝዋ ያየችው የትወና ችግሮች በዋና ገፀ ባህርያት ሆነ በ ንኡስ ገፀ ባህርያት ቃላቶችን በደንብ ጥርት አድርጎ የመናገር፤የማሰማት ችግሮች፣በአጃቢ ተዋንያን ላይም ትክክለኛ ስሜታቸዉ ከመግለፅ ይልቅ አስመስሎ የመተወን ችግሮች ከተመስጦ የመዉጣት ስሜት እና ድምፅ በደንብ ጥርት አድርጎ የመናገር ችግሮች ተስተዉሏል። በአጠቃላይ ስንብት ፊልም በተመስጦ፣ውስጣዊ ፍቺ፣ስሜት፣ማስተዋል እና ከድምፅ አወጣጥ ትወና አንፃር ሲተነተን በጣም የተዋጣለት እና ወደፊት ለሚሰሩ ፊልሞች ትልቅ የትወና ትምህርት የሚሆን ድንቅ ተደርጎ የተሰራ ፊልም ነዉ።

## 4.2 የመፍትሔ ሀሳብ

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ ስንብት ፊልም በምታጠናበት ወቅት በፊልሙ ላይ ተመስጦ፣ዉስጣዊ ፍቺ፣ስሜት፣ማስተዋል፣ድምፅ አወጣጥ በአግባቡ ከመጠቀሙ አነፃር ጥቂት ክፍተቶችን ለመመልከት ችላለች። እነዚህ ክፍተቶችን ቢቀረፉ ብላ ያሰበቻቸዉ የመፍትሔ ሀሳቦች እንደሚከተለዉ ታስቀምጣለች።

ስንብት ፊልም ከስሜት ትወና አንፃር በምንመለከትበ ጊዜ የዋና ገፀባህሪዉ የስሜት አተዋወን በ ጥሩ ሁኔታ የተተወነ ሲሆን አጃቢ ተዋንያን ላይ ግን ስሜታቸዉ የመቀዝቀዝ እንዲሁም የማስመሰል ስሜት ይታይባቸዉ ነበር። አጃቢ ተዋንያን ስሜቱን ተላብሰዉ ቢተዉኑ ፊልሙ ይበልጥ ጠንካራ ይሆን ነበር። የድምፅ አወጣጥ ላይ በምንመለከትበት ጊዜ አንዳንድ ትዕይንቶች ላይ መሪ ተዋናይ ሆነ አጃቢ ተዋናይ የሚናገሩት ቃላት ጥርት ብሎ አይሰሙም።

ድምፅ ለትወና አስፈላጊ ስለሆነ ተዋናዮቹ በሚተዉኑበት ጊዜ ድምፃቸዉ ማሰማት ነበረባቸዉ።ይህም ፊልሙ ጠንካራ ይሆን ነበር። በአጠቃላይ ፊልሞች ሲሰሩ በፊልም ትወና ላይ የሚሳተፉ ተዋንያኖች በቂ እዉቀት እና ልምድ ቢኖሯቸዉ የተሻሉ ስራዎች መሰራት ይቻላል።

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. The Art of Concentration focuses your attention, not on yourself but on the emotions of the other actor. ጀርሚ ኮሚ / 2002 ገጽ 30 / « The art of film acting » (1)

2. vocal production and projection take precedence over the emotional moment when speaking. For the actor on film, the emotional moment and its nuances take precedence. ጀርሚ ኮሚ / 2002 ገጽ 31/ « the art of film acting » (2)

.

## ዋቢ መጽሐፍት

ሰለሞን ሀይሌ መኮነን (2007) የፊልም ጥበብ ገበታ ። አዲስ አበባ ፣ ዱዳሄ ማተምያ ቤት ።

ሳሙኤል ተስፋየ (2010) የትወና ጥበብ ።አዲስ አበባ

ብርትኳን አሻግሬ (2013) ከደመና በላይ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አለባዊያን አንፃር ። ወልቂጤ ዩንቨርስቲ ፣ ያልታተመ የአርትስ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ።

ነብዩ ማሞ (2013) ተፈጣሪ እና ሰባ ዘጠኝ ፊልሞች ከፊልም ትወና ጥበብ አንፃር ። ወልዲያ ዩንቨርስ፣ ያልታተመ የአርትስ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ።

አለም እሸቱ (1994) መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ።የቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋክሊቲ ህትመት።አዲስ አበባ።

ግሩም ኤርምያስ (2001) የትወና መሰረታዊ መመሪያዎች ።አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት

ወሰንየለህ ጥላሁን (2005) የፊልም ጥበብ ቅኝት።አዲስ አበባ፣ፋርኢስት ትሬዲንግ ሀ, የ, የ, ግ, ማህበር።